

# ጳውሎስ

- ሳውል ክርስቲያኖችን የሚጠላና የሚያሳድድ ክፉና ጨካኝ ሰው ነበር።

- አንድ ቀን ሳውል በደማስቆስ ምኩራቦች ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖችን ለማሰር ወደዚያው ተጓዘ። ምኩራብ በአይሁዳውያን የሚሰራና እግዚአብሔርን ለማምለክና መንፈሳዊ ትምህርቶችን ለማስተማር የሚያገለግል ሕንፃ ነው። ከዚያም አስደናቂ ነገር ሆነ። በመንገድ ላይ እያለም የሚያስበው እንዴት ክርስቲያኖችን መጉዳት እንደሚችል ብቻ ነበር። ወደ ደማስቆ እየተጠጋ እያለም ከሰማይ በድንገት ደማቅ ብርሃን በዙሪያው አበራ።

- ሳውል በመሬት ላይ ወድቆ ተደፋ። አንድ ድምፅም "ሳውል፣ ሳውል፣ ለምን ታሳድደኛለህ?" አለው። ያ ድምፅም በመቀጠል "እያሳደድከኝ ያለኸው እኔ ኢየሱስ ነኝ። ከእኔ ጋር ተዋግተህ አትዘልቀውም። አሁንም ወደ ደማስቆ ሂድና ማድረግ የሚጋባህን ሰዎች ይነግሩሃል።"

- ሳውል ከመሬት ሲነሳ አይኖቹ አያዩም ነበር። ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች እጁን ይዘው ወደ ከተማ አስገቡት። ለሶስት ቀናት የጳውሎስ አይኖች አያዩም ነበር። ምግብ መብላትም ሆነ ውኃ መጠጣት አይችልም ነበር።

- እግዚአብሔርም በሕልም ሐናንያ የሚባለውን ሰው ወደ ሳውል እንዲሄድ ነገረው። ሐናንያም ሳውል ወዳለበት ቤት ሄዶ እጁን ጭኖ ፀለየለት። ሳውልም ማየት ጀመረ። ከዚያም ሐናንያ ሳውልን እንዲነሳና እንዲጠመቅ ከኃጢአቱም እንዲነፃ ጠየቀው።

- ሳውልም ሲያደርግ በነበረው ነገር ሁሉ ተፀፀተ። ከዚያም ቀን ጀምሮ ኢየሱስ የሚሻውን ነገር ብቻ ለማድረግ ወሰነ። አደረገም። የሳውል ሕይወት ከተለወጠ በኋላ ስሙም እንዲሁ ተለወጠ። በቀረው የሕይወት ዘመኑም ኢየሱስን ማገልገልና ለሌሎች እርሱን መስበክ ኑሮው ሆነ። በአለም ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ የወንጌል መልእክተኛ ሆነ። ጳውሎስ አሳዳጅ እንዳልነበር ሁሉ አሁንም በተራው በኢየሱስ ላይ በነበረው እምነቱና በአገልግሎቱ ምክንያት ብዙ ስደት ደረሰበት።

የሳውልን መለወጥ በአዲስ ኪዳን በሐዋርያት ሥራ በምዕራፍ 9፡ ከቁጥር 1 – 19 ድረስ ማንበብ ይቻላል።

http://gardenofpraise.com